**ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ**

**Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity**

Efdpu@aol.com www.Finote.org

ፕሮግራም፥ ረቡዕ እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሶስት ሰአት በ 25 ሜትር ባንድ

Programm. Wednesday and Sunday 8.00 PM — 9.00PM on 25 meter band

*የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ*
*መጋቢት 9 ቀን 2007 ዓ.ም. የተላለፈ*

# አይሆንምን ትተሽ ይሆናልን ባሰብሽ !

እንደ ምዕራባውያን የቀን አቆጣጠር፤ በማርች 9 ቀን 2015 ( መጋቢት 1 2007 ዓም) በኬንያ ዋና ከተማ ናይሮቢ ውስጥ የወያኔ መሪዎችና ራሱን የኦጋዴን ነፃ አውጭ ግንባር ( O. N.L. F ) ብሎ የሚጠራውና በትውልደ ሶማሊያን የሚመራው አማፂያን ድርጅት መሪዎች ስብሰባ አካሄደዋል ። የስብሰባው ዋና ዓላማ፤ "የኦጋዴን ሶማሌዎች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የሚውስኑበትን መብት ለማስከበር " እንደሆነ የእንቅስቃሴው ቃል አቀባይ አብድራህማን ማህዲ ገልጿል።

የወያኔውን ህገ መንግሥት አንቀፅ 39ን በመጠቀም፤ ተግባራዊ በማድረግ የወደፊቱን እዳላቸውን ለመወሰን እንደሆነም ጨምሮ አስታውቋል። የዚህ የናይሮቢ ስብሰባም፤ በዚህ ወሳኝ ጉዳይ ተነጋግሮ ከአንድ ስምምምነት ላይ እንደሚደርሱም በመቋመጥ የታጀበውን ምኞቱንም ገልጿል ።

የኦጋዴን ነፃ አውጭ ግንባርና የወያኔ መሪዎች፤ ከግንቦቱ ምርጫ በፊት ይህን ውይይት ለማደረግ ለምን እንደተነሳሱ የተለመደውን ጥርጥሬ ማስከተሉ የማይጠበቅ አልነበረም ። ከራሳቸው ስትራተጂያዊ ዓላማ ጋር የሚደጋገፍ በመሆኑ፤ ጡት የሚጠባው ህጻን ሳይቀር የሚስተው አይደለም ። ኦጋዴንን አስገጥሎ፤ የትግራይን ነጻ ሀገር ለመመስረት የቅድሚያ ዝግጅት ሽር-ጉድ እንደሆነ ልንስተው የሚገባ አይሆንም። " አይሆንምን ትተሽ፤ ይሆናል ባሰብሽ " ብለው ካላሰቡ፤ ትላንት ኤርትራን ያስገነጠለ ቡድን፤ ነገ ኦጋዴንን አያስገነጥልም ብሎ እንዝህላል መሆን ትርፉ፤ ኋላ፤ ወየው! ወየው! ሆኖ ይቀራል።

ወያኔ የተመሰረተበትን 40ኛ ዓመት ለማከበር ባለፈው የካቲት ወር በመቀሌ ከተማ አንድ መቶ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በፈጀ ድግስ ተከናውኗል ። የአምስት ሀገር መሪዎች፤ ማለትም ፤ የሱዳኑ ፕረዝዳንት ኦማር ኤል በሽር፤ የሩዋንዳው ፕረዝደንት፤ ፖል ካጋሜ፤ የሶማሊያው ፕረዝዳንት፤ ሀሰን ሸኽ ሞሃመድ፤ የጅቡቲው ጠቅላይ ሚንስትር ካማል አብደርቃድር ሞሃመድ፤ የዩጋንዳው ጠቅላይ ሚንስትር ሩሃካና ሩጉንዳ መቀሌ ከተማ ተግኝተዋል ። የወቅቱ የአፍሪካ ኅብረት ሊቀ መንበርት የሆኑት ወይዘሮ እንኮዛና ድላሚኒ ዙማም በድግሱ ላይ ነበሩ ። የወያኔ መሪዎች፤ በኢትዮጵያ አንጡራ ገንዘብ የራሳቸውን ድግስ አዘጋጅተው ፤ ሰርግና ምላሻ አውጥተውብታል ። በምንሊክ ቤተመንግሥት ዙሪያ፤ በረሀብ አልንጋ የሚገረፈውን ችግረኛ ግን እናቱ ትቁጠረው !

ከላይ የተዘረዘሩት እነኝህ የሌላ ሀገራት መሪዎች፤ በግለሰብ ደረጃ ደግስ ላይ ተግኝቶ አስረሽ -ምችው ቢሉ የየግላቸው ወሳኔ ነው ማለት ይቻል ይሆናል ። ግን ከተለምዶው የዲፕሎማቲክ አሰራርና ሥነስርዓት ውጭ በሆነ መንገድ የኢትዮጵያን ሀገራዊ ሉዓላዊነት የደፈረ መሆኑን በሚገባ ሊያጤኑት በተገባ ነበር ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ይህንን ድፈረት በአግባቡ አስመዝግቧል። ኢሕአፓም በበኩሉ፤ በየካቲት 26 ቀን

2007 ዓም (በማርች 5 ቀን 2015 ) በተመዘገበ ደብዳቤ ለአፍሪካ ኅብረት ሊቀ መንበርት አሳውቋል። በአፍሪካ ኅብረት ባኅረ- መዝገብም እንዲሰፍር አደርጓል።

ካላይ የተዘረዘሩት የአምስት ሀገሮች መንግሥታት መሪዎች፤ ከአንድ ኢትዮጵያን በማፈራረስ ላይ ከሚገኝ ቡድን ጋር መተባበር፤ የዲፕሎማቲክ ጸያፍ ተግባር መሆኑን ሊረዱት በተገባ ነበር። በሀገራችን የውስጥ ጉዳይ ሊገቡም ባላስፈለጋቸውም ነበር። ተገነዘቡትም አልተገነዘቡትም፤ ታሪካዊ ስህተትም ፈጽመዋል። ድርጊታቸው፤ በማነኛውም ዲፕሎማቲክ ወግና ልምድ የሚነቀፍ እንጅ የሚደገፍ አይሆንም ። ዛሬ፤ በሀገራችን ላይ በተደጋጋሚ የሚፈጸመውን ግፍ፤ በደልና ጥቃት እየተከታተሉ መቃወምና ማስመዝገብ የትግላቸን ዓላማ በመሆኑ፤ ይህንኑን እያሳወቅን እንቀጥላላን ። ይህ ጥረታችን ደግሞ፤ የኢትዮጵያን ሀገራዊ ጥቅም የሚያስጠብቅ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እስከ ተመሰረተ ድረስ ይቀጥላል ።

ወያኔ፤ የተፈጠረበትን 40ኛ ዓመት ለማክበር፤ ይህንን ሁሉ ሽብ-ረገብ ያደረገበት የራሱ ምክንያት አለው። ይህ ምክንያት፤ የሀገሪቱን ፖለቲካ በቅርብ ለሚከታተሉ ጠቢባንና የፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆን፤ ለማንም አልፎ-ሃጅ ታዛቢ እንኳን ሳይቀር የተሰወረ አይደለም ። ለአለፉት 24 ዓመታት የሥልጣን ዘመኑ ፤ ለመጨረሻ ዓላማው ጉዝጓዝና መደላድል የሚሆነውን ሁሉ ሲያከናውን ቆይቷል። ከሞላ- ጎደል፤ የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባሮች አከናውኗል ።

1ኛ. የትግራይን ክፍለ ሀገር የቆዳ ስፋት ቀድሞ ከሚታወቀው ሁለት እጥፍ በላይ አስፍቶ ጨምሮታል ። ይህንንም ያደረገው ከጎንደር ፤ ከወሎና ከአፋር መሬቶች በኃይል በመንጠቅ ነው ። እንደ ቅኝ ዥዎች የግዛት ማስፋፋት ዓላማውን ፈጽሟል ። ነዋሪዎችንም እንደ ቅኝ ግዛት በግፍ እየበደለና እየጨቆነ ይገኛል። ተቃዋሚዎቹንም ፈጅቷቸዋል። የዘር ማጥፋት ወንጀል ፈጽሞባቸዋል። ቀሪዎቹንም በወኅኒ እንዲማቅቁ አድርጓቸዋል። ከሞት የተረፉትንም ለስደት ዳርጓቸዋል። ታሪክ አዋቂዎቹንም አጥፍቷቸዋል ። ጀግና ጠፍቷል። ወጣቱ ተሰድዷል ። ሀገር መና ቀርቷል ። በዘር ጥላቻ መንሰዔ ክልቡ የሚጠላውንና የሚፈራውን የጎንደርን ሕዝብ ፤ ለጊዜውም ቢሆን አንገቱን አስደፍቶታል ። አዝማሪውም **" እነርሱ ምን ያድርጉ ከኛ ሰው ሲታጣ ! " እያለ ይማልላል ። ያለቅሳል። ያስለቅሳል ። ይቋምዛል ።**

2ኛ. የወያኔው ትግራይ "መንግሥት" ግዛት ዓለም አቀፍ ድምበር { ወሰን} እንዲኖረው አድርጓል ። ከጎንደር ክፍለ-ሀገር አንስቶ እስከ ወለጋ ክፍለ-ሀገር ያለውንና ከሱዳን ጋር የሚያዋስነውን ሰፊ የኢትዮጵያ ግዛት፤ ከሱዳኖች ጋር ተመሳጥሮ፤ ወደፊት ለሚያውጀው አዲስ ሀገር፤ የዓለም አቀፍ ወሰን/ ክልል ዘርግቶ አረጋግጧል ። ለባኅር ወደብ የሚጠቅመውን የመገናኛ መስመር ዕውን ለማድረግ፤ ከጅቡቲ እስከ ትግራይ ክልል የመገናኛ መስመር እየዘረጋ ይግኛል። ወደፊት ከኤርትራ ጋር ስለሚኖረው ውኅደትና ግንኙነት የሚያስፈልገውን ውይይት በማድረግ ላይ እንደሆነ የአደባባይ ምሥጢር ሆኗል።

3ኛ. ከኢትዮጵያ አስግንጥሎ ለሚመሰርተው አዲስ ሀገር ሊጠቅም የሚችል፤ የተማረ ሰፊ የሰው ኃይል እያዘጋጀ ነው ።ይህንን የሚያከናውነው ደግሞ የኢትዮጵያን ግዙፍ ሀብት በመጠቀም ነው ። የሕዝቡንም ቁጥር በሚያስገርም ፍጥነት እየጨመረው ነው ። ይህም ትግራይ ኅዳጣን መሆኗ ቅርቶ፤ ብዙሃን እንደሆነች ለማሳመን የሚደረግ ጥረት ነው ።

4ኛ. መቐለን፤ የአዲሲቱ ሪፑብሊክ ዋና ከተማና የአካባቢው ዲፕሎማቲክ መናሃርያ ለማድረግ ሁሉም ነገር እየተሟላ ይገኛል። ዓለም አቀፍ አይርፖላን ማረፊያ፤ ታላላቅ የየብስ መንገዶች፤ የባቡር መስመሮች በጥድፊያ በመዘርጋት ላይ ይገኛሉ። ከስድሣ ሽህ በላይ መቀመጫ ያለው ስቴድየም ተጠናቅቆ ተሰርቷል። የወደፊቶቹን የውጭ አምባሳደሮችንና ዲፕሎማቲክ ማኅበረሰቡን የሚያስተናግዱ ታላላቅ ቤቶችና ማዕከላት እየተገነቡ ናቸው ። የምኒልኳን አዲስ አበባ፤ በዮሐንሷ መቐለ ለመተካት ጥድፊያው ተጧጡፏል። አባይ ኢትዮጵያን እየደመሰሱ፤ በዐባይ ትግራይ የመተካት ኅልማቸውን ለማሳካት እየጣሩ ናቸው ።

5ኛ. በኢትዮጵያ ሕዝብ አንጡራ ሀብት የተገነባ፤ የታጠቀና የተደራጀ ሠራዊትና ዘመናዊ የጦር ትጥቅ፤ በትግራይ ውስጥ ስፍሮ ይገኛል። ዘመናዊው የአየር ሃይል ሰፍርና ማዕከል ትግራይ ውስጥ ሆኖ ለነጻነታቸው ዕወጃ ትዕዛዝ ነቅቶ ይጠባበቃል። አደረጃጀቱም፤ ከአንድ ብሄር አባላት በተውጣጣ ዕዝና ቁጥጥር ስር ነው። በዕርከንም ደረጃ ቢሆን፤ ከላይ አዛዦች ጀምሮ፤ እስከ ዝቅተኛው የሠራዊት አካል ድረስ በትግራይ ተወላጆች ጥብቅ ቁጥጥር ስር ሆኖ ተዋቅሯል።

6ኛ. በኢኮኖሚ በኩልም የተደረገው ቅድመ-ዝግጅት፤ሁሉንም የሚያስደምም ሆኗል ። ይኸውም፡-

ሀ. የንግዱን የፋይናንሱን ( የገንዘቡን ) የባንኩን፤ የጉምሩኩን፤ የኢንሹራንሱን፤ የአስመጭና ላኪውን እንቅስቃሴ እንዲሁም የፈቃድ ሰጭውን ሥልጣን በቁጥጥራቸው ስር አስገብተውታል፤ ይኸም ፤ ማንኛውንም የሀገሪቱ ሀብት በስፋት ወደ ትግራይ እንዲያጎርፉት አስችሏቸዋል ።

ለ. የመጓጓዣ፤ የመገናኛ፤ የፖስታ-ቴሌፎን- ቴሌግራፍ፤ የኢንተርኔትና ኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት ሰጭ ተቋማትን ተቆጣጥረውታል ። ይህም፤ ሁሉንም ወደ መቐለ የሚለውን ፕሮግራም ማሳኪያ እንዲጠቅም ሆኖ ተቀይሷል።

ሐ. እንደ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች ዓመታዊ ዘገባ ከሆነ፤ ወያኔ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ፤ አስራ አንድ (11) ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር፤ ሀገ-ወጥ በሆነ መንገድ፤ የወያኔ ባለሥልጣናት ወደ ውጭ አንዳስወጡ ተረጋግጧል።

7ኛ. ከላይ የተዘረዘሩት ቅድመ ዝግጅቶች በአሁኑ ወቅት፤ የወያኔዋን ትግራይ፤ ሁሉንም ዝግጅት አጠናቅቃ ያላቀላት ሀገር አድርጎ አስቆጥሯታል ። በተጨባጭ ሪፑብሊክ አድርጓታል ። አሁን ወያኔዎቹ የሚጠባበቁት አንድ ጉዳይ ብቻ ነው ። ይኸውም ፤ የሚመቻቸውን ጊዜ ሲያረጋግጡ ፤ በህገ አገዛዛቸው ፤ አንቀጽ 39 መሠረት ፤ " ማንኛውም ብሄር የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰንና እስከ መገንጠል ድረስ የሚያስችለው መብቱ የተረጋገጠ ነው " የሚለውን ጠቅሰው ፤ ሪፑብሊክ ትግራይን ማወጅ ነው ። አሁን የሚቀራቸው የሪፑብሊክ ሁኔታ ወደ " ህጋዊነት " ትግራይ ሪፑብሊክን ማረጋገጥ ይሆናል ።

ይህ የወያኔ ዕኩይ ምኞት፤ ይሳካል አይሳካም ማለት ሌላ ጉዳይ ቢሆንም፤ የእነርሱን የግንጠላ ተግባር ግን በአርምሞ ማየት አይቻልም። እነርሱ ዓላማቸውን ለማሳካት የተቻለውን ሁሉ ቢጥሩም፤ ፈጽሞ ይሳካል ብለን አናምንም ። ይህንንም ስንል የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት በማስገባት ነው። ይህም በአልፋ-ኦሜጋ

ኢትዮጵያዊነቱ አምጡ- ድገሙ የማይባልለት የትግራይ ሕዝብ፤ የወየኔን አጥፊ ተግባር ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሆኖ እንደሚያከሽፈው ምንም ጥርጥር ስለሌለን ነው።

ሀገር-ወዳድ ምሁራንን፤ የሀገሪቱ ፖለቲካ ተንታኞችንና ሀቀኛ የፖለቲካ ድርጅቶችን፤ ምናልባት ከሌላው ሕዝብ፤ ሊለያቸው የሚችል ጉዳይ ቢኖር ፤ የሀገሪቱን ሁለንተናዊ ጉዳይ በቅርበት እየተከታተሉ የሚመጣውን አደጋ ለሕዝብ መግለጽ አንዱ ነው። በመሬት ላይ የሰፈረውን ሀቅ፤ ከአካባቢው ሁኔታዎችን ጋር እያዛመዱ፤ የሀገሪቱን መፃኢ ዕድል ምን ሊመስል እንደሚችል መጠቆምና አማራጩንም መጠቆም አስፈላጊ መሆኑን መረዳት፤ አንገብጋቢ ብቻ ሳይሆን፤ ወሳኝ እንደሆነም እናምናለን።

ይህንንም ተግባር በበኩላችን በሦስቱ ተፈራራቂ ሥርዓቶች ስናደርገው የቆየ የትግል ተመክሯችን ነበር። አሁንም ነው። የዐፄው ሥርዓት፤ ለውጥ ካላመጣ፤ ሀገሪቱ አደጋ ላይ ትወድቃልች ተብሎ ቢነገርው፤ ሰሚ ጠፋና፤ ጊዜው ሲደርስ በሕዝብ ትግል ተሻረ። ደርግ ሥልጣን ሲይዝም፤ ለሀገሪቱ እንደማይጠቅም ተነግሮት፤ ከሕዝቡ የተውጣጣ፤ ጊዚያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ቢመጣ ይሻላል ቢባል፤ ሰሚ ሳይገኝ ቀረ። ከዚያ በኋላ የሆነው የሚታወቅ ነውና ለታሪክ እንተወዋለን ። ወያኔም ወደ አዲስ አበባ ከመምጣቱ በፊት አስቀድመን፤ ይህ ጠባብ ብሄረተኛ ቡድን ኢትዮጵያን ያጠፋታል ብለን አበክረን ጮኸናል ። " ጀሮ ዳባ-ለብስ ተባለ" በአሁኑ ወቅት ፤ ይህንን ተናገረን ነበር ማለቱ ግብዝነት ስለሆነ ያንን አንልም። አሁን ስለሚያንዣብበው አደጋ ግን ማሳሰባችንን እንቀጥላለን ።

ለታሪክ ግንዛቤ የሚረዳ ከሆነ፤ ከአንድ መቶ ሃያ / 120 ዓመት በፊት አንድ የትግራይ ሴት፤ በእንጉርጉሮ ያዳመጣቸውን ሁሉ ያስለቀሱበትን የሀዘን ጸጸት እንጠቅሳልን ።

" ተናግሬ ነበር እኔማ አስቀድሜ

የተሻረው ባሌ ተሿሚው ወንድሜ፤

አሁን ማን ይሰማል ከሀዘን ላይ ቆሜ፤

ኢትዮጵያ ከሌለች አለምንም ዕድሜ ። "

አይሆንምን በመተው፤ ይሆናልን መጠርጠርና አስቀድሞ መፍትሄ እያዘጋጁ፤ ሀገርን ከጥፋት ማዳን የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት መሆኑን ደግመን ደጋግመን እናሳስባለን ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም መኖሯን ትቀጥላለች !